# ተስፋና ስጋት ያንዣበበበት የእኛ ኢትዮፒያዊያን አንድነት

## ክፍል አንድ

እኛ ኢትዮጵያውያኖች ባለፉት ሃያ አመታት በአንድነት ቆመን ለመብታችን ከመሟገት ይልቅ አንዳችን የሌላኛውን ወገናችንን ውድቀት በጉጉት በመጠበቅ ረዥም ወቅት በማሳለፋችን ምክንያት ጨቋኞች በስልጣን ተደላድለው፣ ማንነታችንን አዋርደው እንዲገዙን መፍቀዳችን አንገት የሚያስደፋ ጉዳይ ነው።

ያለፉትን 23 አመታት መለስ ብለን ከቃኘን ለህግ አልገዛም ባሉ መሪዎች የጋራ ጥቅማችን ተነጥቆ መብታችን ተገፎ ክፉኛ እየተበደልን የምንገኝ ቢሆንም በተሰለፍንበት ጎራ ለጋራ ጥቅም በጋራ ከመቆም ይልቅ ከፊሎቻችን ፡ -

- የግል ወይንም የቡድን ጥቅምን ከጋራ አገራዊ ጥቅም በማስቀደም ለአምባገነኖች መሳሪያ በመሆን አንዳችን የሌላኛችንን መብት በመርገጥ እና በማስረገጥ ድርጊት በመሳተፋችን ጥቂት ለህግ የማይገዙ መሪዎች የዜጎቻችንን መብት እንዲገፉ አስችለናል። ይህ ደካማ ባህርያችን ለአምባገነኖች መብት መርገጥን በመፍቀዱ ሃገራችን ወደ አሳፋሪ ደረጃ እንድትወርድ የድርሻችንን አበርክተናል።

- አምባገነኖች በአመለካከት ፣ በእምነት ወይም በዘር ከእኛ የሚለዩ ወገኖቻችንን መብት ሲረግጡ ድርጊታቸው ተገቢ መሆኑን በመግለጽ የወገኖቻችን መብት መግፈፍ አግባብነት ያለው ድርጊት መሆኑን በማመላከታችን ራሳችንን ለጥቃት ዳርገናል

- አምባገነኖች የህዝባችንን መብት ሲረግጡ በፍርሃት በመረታት ድርጊታቸዉን ከማውገዝ ይልቅ የሚያደነቁር ዝምታ መርጠናል። በዚህም የህዝባችን መብት መገፈፍ አግባብነት ያለው ድርጊት መሆኑን በማሳየት ራሳችንን ከበዳዮች ተራ አሰለፈናል

- ዜጎች በሚገልጹት አቋም እና በድርጊታቸው በመዳኘት ህግመንግስታዊ መብቶቻቸው እንዲከበሩላቸው ስጠይቁ እንቅስቃሴያቸዉን በመደገፍ ለህግ የበላይነት በሃገራችን መስፈን በጋራ ከመቆም ይልቅ የእንቅስቃሴያቸውን አላማ አጣመን በማቅረብ ህዝብ እንዲከፋፈል እና ያለመተማመን እንዲነግስ በማድረጋችን የልብ መራራቆችን ፈጥረናል።

ከቅርብ ግዜ ወዲህ ግን እንደተለመደው ግብታዊ በሆነ መንገድ ወደ አንድነት መምጣት አለብን የሚሉ ድምጾች መስተጋባት ጀምረዋል። ሆኖም በተቀናጀ እና በተጠና መንገድ ካልተካሄደ በስተቀር የተለመደው ውድቀት አሁንም ተከስቶ ይበልጥ መራራቅ እንዳይመጣ ስጋት አለ ስለሆነም በዚህም ሂደት ሊያጋጥም የሚችልን ፈተና እና አደጋ መገምገም አስፈላጊ ነው።

የህዝባችን የመከራ ግዜ በመርዘሙ እና የውርደቱ ጫና የመረረ እየሆነ በመምጣቱ ወደ አንድነት ለመምጣት መጣደፍ ይታያል። ይህ እንደ ምኞት መልካም ቢሆንም በተጠና መንገድ ካልተጀመረ እና የፀና መሰረት ላይ ካልተቀመጠ መፍረክረኩ የማይቀር ነው። ስለሆነም ከጅምሩ ተስፋ አስቆራጭ እንዳይሆን ጥንቃቄ ያሸዋል።

በአሁኑ ግዜ በሃገራችን የህግ የበላይነት የሚሰፍንበትን ስርአት ለማምጣት አላማ አለን የሚሉ እና ቀና መንፈስ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ወደ አንድነት ለመምጣት የመጣደፋቸው ሁኔታ ጎሽ የሚያሰኝ ነው። ነገር ግን ካለንበት የችግር አዙሪት ለመውጣት የሚያስችለንን ፍርያማ የሆን የጋራ ጉዞ እንጀምር ዘንድ

- በሰከነ መንፈስ ዝግጅት የተደረገለት
- ችግሮችን ነጥሎ ያወጣ እና ጥልቀታቸውን የመረመረ
- ሁላችንንም የሚያሳትፍ ፣ በእቅድ የሚመራ፣ መመዘኛዎችን ያስቀመጠ ዝግጅት ቢደረግ ከምንፈልገው ግብ እንድንደርስ እገዛ ሊያደርግ ይችላል።

በዚህ አኳያ ችግሮቻችንን ደረጃ በደረጃ ለመቅረፍ እንችል ዘንድ የልዩነት ምክንያቶቻችን ምን እንእደሆኑ አውቀን እና ጥልቀታቸዉንም ተገንዝበን መፍትሄዎችን በጋራ ለመሻት የጋራ ዝግጅት ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ሆኗል።

እስከዛሬ በጋራ አላማ በአንድነት እንዳንቆም ካደረጉን መሰረታዊ ችግሮች አንዱ ***<u>ያለመተማመን</u>*** ወይንም ገደብ የለሽ ጥርጣሬ ስለሆነ ችግሩን በመመርመር የመፍትሔ ሃሳቦችን ለማቅረብ ይሞከራል።

ጥርጣሬ ሁለት መሰረታዊ ዘርፎች አሉት፡- አንደኛው ገደብ የለሽ ጥርጣሬ ወይንም ደግሞ ያለመተማመን ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ሚዛን የጠበቀ ጥርጣሬ የምንለው ነው። ከዚህ በታች የሁለቱን ባህርያት ለመቃኘት ይሞከራል፡-

<u>መተማመን የሰዎች ተፈጥሯዊ ባህርይ ሲሆን መተማመን በሌለበት ግዜ ግን ፍርሃት በብቸኝነት ይነግሳል።</u>

**<u>ሚዛን የጠበቀ ጥርጣሬ</u>**

መጠራጠር በአብዛኛው ግዜ በአፍራሽ ገፅታው የሚታወቅ ቢሆንም ሚዛኑን የጠበቀ ጥርጣሬ በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ይነገራል ። ከሚጠቀሱት ጠቀሜታዎቹ መካከል ያለመተማመንን ደረጃ በደረጃ ለመቅረፍ ማስቻሉ፡-

- የሚታለመው መቀራረብ ገና **ከጅምሩ አንዳችም ጥርጣሬ የማይታይበት ሆኖ ከተወሰደ የሚፈጠረው ህብረት የመተማመንን ግንባታ ሂደትን ደረጃ** ያልተከተለ ይሆናል። ይህ ደረጃን ያልጠበቀ ፣ የችግርን ጥልቀት ያልመረመረ እና የተቻኮለ አካሄድ ውጤት የመሆኑ አንድ አመላካች ሊሆን ይችላል። ይህም ጉዞን በለጋነቱ የመቀጨት እና ተስፋ የማስቆረጥ አደጋ ከማስከተሉ በፊት የተመጣጠነ ጥርጣሬ የሚለውን መርሆ የሚያምኑ ወገኖች መገምገሙ እገዛ ሊያደርግ መቻሉ
- **ሚዛን የጠበቀ ጥርጣሬ ግለሰቦችም ሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ነገሮችን በጥንቃቄ እንዲመለከቱ ስለሚያስችል** <u>**የመተማመን መንፈስን** ለመገንባት የሚደረግን ጥረት በረጋ መንፈስ እንዲሰራበት ሊያግዝ እንደሚችል ይታመናል</u> ።

***አንድ ማህበረሰብ በተለይ ለረዥም ዘመናት ከተቆሳሰለ ቡሃላ ወደ አንድነት እንዲመጣ ከተፈለገ የጉዞውን እርምጃ ረጋ ባለ መንፈስ በመርህ ላይ በተሞረኮዘ መልክ ደረጃ በደረጃ መተማመንን እየገነባ መሄድ ይጠበቅበታል። ለዚህ አይነት ጥንቃቄን ለሚሻ ሂደት ሚዛን የጠበቀ ጥርጣሬ መኖሩ ተከስተው የነበሩ ቁርሾዎችን በየደረጃ ፈውስ ለመሻት የሚደረግን ጥረት ፍርያማ ሊያደርግ ይችላል ።***

- ሚዛን የጠበቀ ጥርጣሬ መኖሩ ግለሰቦች የሚቀርቡላቸውን ጉዳዮች በየዋህነት ከመመልከት ወይም ከመከተል ይልቅ በሰላ አዕምሮ አይተው ሚዛናዊ ውሳኔ እንዲወስዱ የሚያግዝ ከመሆኑም በላይ በጭፍን የቡድንን ሃሳብ ተከትሎ ውሳኔዎችን ከመወሰን እንዲቆጠቡ ይረዳል።

- ሌላው ሊጠቀስ የሚችለው ጠቀሜታው ቀደም ሲል ተቋስለው የነበሩ ቡድኖች ሚዛን በጠበቀ ጥርጣሬ ላይ በመሞርኮዝ የሚፈጥሩት ግንኙነት የተረጋጋ እና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ስለሚያደርግ መፋረስ እንኳን ቢመጣ የሚያስከፍለውን ዋጋ አነስተኛ ያደርጋል። በተለይም በፖለቲካ አለም ይህ አይነት ጥንቃቄ የተሞላበት ጉዞ አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል። ለረዥም አመታት ተራርቆ ወደ አንድነት በሚመጣበት ግዜ ፍትህ የሚሰፍንበትን ወቅት ለማቅረብ ጉጉት ስለሚኖር ሚዛኑን የጠበቀ አካሄድ በመከተል ደረጃውን የጠበቀና ጤናማ የሆነ መተማመንን መገንባት ያስችላል።

- ሚዛኑን የጠበቀ ጥርጣሬ በግለሰቦችም ይሁን በቡድን መሃከል ሲንፀባረቅ የሚኖረውን ግንኙነት ሚዛናዊ እንዲሆን ያደርገዋል። ይህም ሚዛንን የጠበቀ ግንኙነት ዘላቂ የሆነ አንድነትን ለመፍጠር መሰረት የሚሆን እና ደረጃ በደረጃ እየተገነባ ከሰው ስነ-ልቦና ጋር በሚጣጣም መልክ ከግብ የሚያደርስ ረዥም ጉዞ ለመጓዝ የሚያስችል እንደሆነ ይታመናል።

<u>ገደብ የለሽ ጥርጣሬ ወይንም ያለመተማመን</u>

በማህበራዊ ግንኙነት የሰዎችን የመኗኗር ፍላጎት የሚመርዘው እና በትግል መስከ መከፋፈል እንዲሰፍን ጠንቅ ሆኖ የሚታየው ያለመተማመን ወይንም ገደብ የለሽ ጥርጣሬ በመባል የሚታወቀው ነው። የዚህን እጅግ ውስብስብ የሆነ በግለሰቦች ፣ በተቋማት ሆነ ባጠቃላይ በማህበረሰብ መካከል ለጋራ ጥቅም በጋራ መቆምን በመሸርሸር ክፍተት እንዲሰፋ የሚያደርግን የዚህን ችግር መንስኤዎቹን ግልጽ እና ሆነ ስውር ባህርያቱን ማወቁ እጅግ አስፈላጊ ነው።

***<u>ለመሆኑ በተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎች መከከል ያለመተማመን ወይንም ገደብ የለሽ ጥርጣሬ ሰፍኗል የሚባለው መቸ ነው ?</u>***

አንድ ቡድን ወይም ማህበረሰብ ያለመተማመን ወይንም ገደብ የለሽ ጥርጣሬ ሰፍኖበታል የሚያሰኘው

ሀ) አንዱ ወገን የሌላኛው ወገኑ እንቅስቃሴ የእሱን ጥቅም ለማጉደል እና እሱን ጉዳት ላይ ለመጣል የሚደረግ አድርጎ ሲውስድ እና በሙሉ ልብ የሚያምን ሲሆን

ለ) አንዱ ወገን የሌላኛው ወገኑ እንቅስቃሴ የእሱን ጥቅም ለማጉደል እና እሱን ለመጉዳት የሚወሰድው እርምጃ በማስመሰል ለሌላኛው ወገን የራሱን መብት እና ጥቅም ለማስከበር የሚያደርገዉን እንቅስቃሴ ከጅምር ለመግታት ሲጥር ነው

ሀ) **<u>የአንዱን ወገን እንቅስቃሴ ሌላኛው እሱን ጉዳት ላይ ለመጣል የሚደረግ ጥረት ነው ብሎ ከሙሉ ልብ ሲያምን የሚከተሉት ባህሪዎች ስንጸባረቁበት ይስተዋላሉ፡-</u>**

- ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉ የጋራ ጥንቃቄ የሚፈልጉ risk አዘል የጋራ እርምጃዎችን ወስዶ በአንድነት ለጋራ ጥቅም መቆምን ለመቀበል ዝግጁ ያለመሆን
- ለአጠራጣሪ ነጥቦች የላቀ ስፍራ በመስጠት በጋራ መስራት ያለውን ጠቀሜታ ማስተባበል እና ወደ አንድነት ለመምጣት ያለውን ጎዳና በማጥበብ በብቸኝነት መስራትን አዋጭ አድርጎ ሲወስድ
- ችግሮችን ለመፍታት ከመጣር ይልቅ ጣት መቀሳሰርን ስራዬ ብሎ ሲይዝ
- በስርአቱ እየተበደለ ያለዉን ፣ የተበደለውን እና ተብድየ ነበር የሚለውን ወገን ብሶት ለመረዳት ጥረት ያለማድረግ
- ተበድያለሁ ባይ ብሶቴን ለወገኖቼ ባካፍልም ለውጥ አያመጣም ከሚል ግምት ወገኑን ሊያሳስቡ የሚችሉ ጉዳዮችን ከማሳወቅ ችላ ማለት

ለ) አንዱ ወገን የሌላኛው ወገኑን እንቅስቃሴ እሱን ለመጉዳት የሚወሰድ እርምጃ በማስመሰል ለሌላኛው ወገን የራሱን መብት እና ጥቅም ለማስከበር የሚያደርገዉን እንቅስቃሴ ከጅምር ለመግታት ሲጥር

- የሌላኛውን እርምጃ ዘወትር በጥብቅ በመከታተል እና ለእያንዳንዱ እርምጃ አፍራሽ negative ፍቺ በመስጠት በራሱ ስሜት ላይ የተመሰረተ መላምትን ለማረጋገጥ የሚሻ ያካሄድ ስልት መከተል
- ዘዎትር በልዩነቶች ላይ በማተኮር እና ያለ ገደብ ልዩነቶችን በማጉላት በጋራ የመቆምን ተስፋ የሚያቀጭጩ ድርጊቶችን በቋሚነት ማራመድ
- በሌላው አካል የተፈፀሙ ወንጀሎችን እና ስህተቶችን ከልክ በላይ በማጉላት እንዳይዘነጉ ምክንያት እየፈጠሩ ደግሞ ደጋግሞ በማስታወስ ቀና አመለካከት ያላቸውን ስጋት ውስጥ በመጣል ለጋራ ጥቅም በጋራ የመቆምን ተስፋ ለማጨለም ተግቶ መስራት
- አብላጫ ህዝብ የማይወክሉ ጥቂት ወደ ጫፍ የወጡ ግለሰቦችን ወይንም ቡድኖች ድርጊቶችን ፣ ንግግችን ወይንም መልእክቶች የሌላኛው ወገን አብላጫ ህዝብ አቋም በማስመሰል በማቅረብ መተማመን እንዳይኖር ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ
- በተለየ ነባራዊ ሁኔታ እና የታሪክ ቁርሾ ባላቸወ ሌሎች አገሮች የሚፈጸሙ አስከፊ ድርጊቶችን ለማህበረሰቡ ማስፈራሪያነት በመገልገል ያለመተማመንን ስር እንዲሰድ ጥረት በማድረግ ወደ አንድነት መምጣት እንደማይቻል በመለፈፍ በአደገኛ ሁኔታ የማህብረተሰብ አባላትን በጋራ የመስራት ችሎታ መሸረሸር ።

- አንድ የማህበረሰብ ክፍል ከእሱ የተለዩ እይታ ያሉዋቸዉን ዜጎች ለሃገራቸው የማይቆረቆሩ አድርጎ መክሰስን ልምድ አድርጎ በመያዝ እራሱን ብቻ የሃገር ተከላካይ አስመስሎ ሲያቀርብ ሌላኛው በሃገሩ የእኩል ባለቤትነት መብቱ እንደተጣሴ በመገመት መራራቅን መምረጥ

- በተወሰኑ ሁኔታዎች ስር እራሱን ለሃገር ብቸኛ ተቆርቋሪ አድርጎ የሚያቀርበው አካል የሌላኛውን ወገኑን የመብት ጥያቄ የሃገርን ደህንነት የሚጎዳ አድርጎ በመውሰድ በአምባገነን መሪዎች የሚወሰደውን የመብት ገፈፋ ከማውገዝ በመቆጠብ የበደል ተባባሪ ሆኖ የሚታይ ሲሆን። ይህ ክስተት በታየ ግዜ ሌላኛው ወገን በተራው የሃገር ተቆርቋሪ ነኝ የሚለውን ወገኑን ውድቀት እና መበደል ለማየት መጓጓት እና ለአምባገነኖች መሳርያ ሆኖ የሱን ጥቃት ማመቻቸቱ ።

- ከዚህ በከፋ ሁኔታ ደግሞ ለሃገር ተቆርቋሪ ነኝ የሚለው አካል ሌሎች ወገኖች የመብት ጥያቄ ባቀረቡ ግዜ ከአምባገነኖች ጎን በመቆም የነሱን ጥያቄ መፈታተን እና ማዳከም ስታይበት። በአጸፋው ሌላኛው አካል በተራው ለአምባገነኖች መሳርያ ሆኖ ይህንን ማህበረሰብ ሲያጠቃ እና ውድቀቱ እንዲጣደፍ ተግቶ በመስራት ላይ ሲሰማራ ።

- ለሃገር ብቸኛ ተቆርቋሪ ነኝ ባዩ ሌላኛው ወገን ለሃገሩ ማድረግ ያለበትን እና መክፈል የሚኖርበትን መስወአትነትን እየለጠጠ ሁሌም በቂ አይደለም የሚል ሃሳብ በማቅረብ የራሱን ማንነት ትቶ እሱን እስኪሆን ድረስ መተማመን እንደሌለ መልእክቶችን የሚያስተላልፍበትን ሁኔታ እንዲፈጠር ሲያደርግ

- እንድህ አይነት ያለመተማመን በምኖርበት ግዜ ግለሰቦች የምቆጠቡት ሃሳብን ከመለዋወጥ እና የተለያዩ ሃሳቦችን ከማንሸራሸር ብቻ ሳይሆን  በአካልም በተወሰኑ ስፍራዎች ላይ በጋራ ከመገኘትም ጭምር ስለሚሆን የልቦና መራራቅ ስር እንዲሰድ ያደርጋሉ።

## <u>ለተፈጠረው ያለመተማመን ምክኒያቶች</u>

- በሃገራችን ለዘመናት ተንሰራፍተው የነበሩት የተዛቡ ስርአቶች አስከትለውት የነበረው ሚዛን የሳተ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ስርአት የሃገርን ባለቤትነት ለዘመናት ከአንድ የህዝባችን አካል የወጡ ሊሂቃንን ብቻ በሞኖፖል እንድይዙት ማድረጉ ነው። ከዚህ የብቸኛ ባለበትነት ስሜት በመነሳት አንዳንድ ከዚህ ማህበረሰብ የወጡት ወገኖቻችን እራሳቸውን ብቻ የሃገር ተቆርቋሪ አድርገው ማቅረባቸው ሌላኛዉን ወገን በሙሉ መንፈስ ለአንድነት ከመቆም እንዲያፈገፍግ ማድረጉ

- ለዘመናት ተገልሎ ከነበሩ ህዝቦች አብራክ የወጡ ሊሂቃን እና የማህበረሰብ አባላት በሃገራችን ኢትዮጵያ የጋራ ባለቤትነት መብት መጠየቅ መጀመር በብቸኝነት ይዘው ለነበሩት አንድንድ ሊሂቃን ባለመመቸቱ ያለመተማመን ሰፍኖ ሁለም ወገን ሊጋራ ጥቅም በጋራ ከመቆም ይልቅ መጠላለፍ ላይ እንድያተኩር መገፋፋታቸው

- እውነተኛዉን የሃገራችን ታሪክ ያለማወቃችን የአንዱን ህዝባችንን እምነት እንደ ሃገር በቀል ለሎች እምነቶችን የባኢድ አስመስሎ በማቅረቡ የተለያዩ እምነት ተከታዮች በሙሉ ልብ ለመቀራረብ ግዜ ወስዶባቸዋል ዛሬም ቢሆን ያለው ችግር የመቀነስ መልክ አይታይበትም
- በዘመናችን የዲሞክራሲ ጭላንጭል መታየት እና በመገናኛ ብዙሃን መስፋፋት ምክንያት ዜጎች ስለ ማንነታቸዉ asertive መሆን መጀመራቸው ቀደም ሲል ጎላ ያለ ስፍራ ይዘው በነበሩ ልህቃን እንደ ጽንፍ የወጣ አመለካከት ተደርጎ መቅረቡ
- በሃገራችን የተሻለ ማህበራዊ እርከን ላይ አሁን ያለው ያገኘውን ብልጫ የማጣት ስጋት

ያለዉን ልዩነት ሊያሰፋ ይችላል በሚል ስጋት ችግሮችን ግልጽ አድርገን በመገምገም መፍትሄ ከመሻት ይልቅ ማድባስባስን ስለመረጥን ችግሮቻችን ከዕለት ወደ እለት ስር እየሰደደ መጥቷል። ስለዝህ ይህን ወደ ወድቀት የምያመራ አካሄዳችንን በመቀየር ችግሮችን በግልጽ በማስፈር የጀመርን ሲሆን በክፍል ሁለት የመፍትሄ ሃሳቦችን ለማቅረብ ይሞከራል።

## <u>ተስፋና ስጋት ያንዣበበበት የእኛ ኢትዮጲያዊያን አንድነት</u>

## <u>ክፍል ሁለት</u>

**በማህበረሰባችን ውስጥ ለጋራ ሙብት እና ጥቅም በጋራ ለመቆም የተሳነን በመሆኑ በሃገራችን ፍርድ ተጓድሎ ወገኖቻችን ሲሰቃዩ እና ሲዋረዱ እየተመለከትን እንገኛለን ።** በክፍል አንድ ለጋራ ሙብት እና ጥቅም በጋራ ላለመቆም ካበቁን በርካታ ችግሮች በቀዳሚነት ሊጠቀስ የሚችለው በመካከላችን የሰፈነው ያለመተማመን ስለ መሆኑ ገልፀናል ። <u>ያለመተማመን እና ተያያዝ ችግሮችን በጋራ ለመቅረፍ በሁለት ደረጃዎች የተከፈሉ መፍትሄዎች እንደሚያስፈልጉ ይታመናል</u>። እነዚህም_

1. ችግሮችን በጋራ ለመ ቅረፍ ለመነሳሳት የሚያስችሉ ዝግጅቶች ላይ ያተኮረ እርምጃዎ ችን መውሰድ
2. ፍትሀዊ እና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ዘላቂ አንድነትን ለመገንባ ት የሚያስችል ሂደትን ስልታዊ በሆነ መንገድ ማከናወን

ከመጀመሪያ ው መፍትሄ ማለትም ችግሮችን በጋራ ለመቅረፍ አነሳሽ ከሆኑ ዝግጅቶች ወደ ዘላቂ መፍተሄ ፍለጋ መሸጋገር የሚኖርበትን ግዜ በትክክል መገመት አዳጋች ቢሆንም የእቅዱ ተግባሪዎች እርምጃዎችን ከስሜት በጸዳ መንገድ መገምገም መቻል እና የጉዞ ስልታቸዉን ጥድፊያ ያልታከለበት እና ደረጃዎችን የተከተለ ማድረግ መቻል ለመፍትሄው ፍርያማነት ወሳኝነት አለው።

1. <u>ችግሮችን በጋራ ለመቅረፍ ለመነሳሳት የሚያስችሉ ዝግጅቶች</u>

**በአንድ ወይም በሌላ የታሪክ አጋጣሚ በተፈጠሩ ስህተቶች የሰፈኑ ቁርሾዎችን የወረሱ የማህበረሰብ ክፍሎች** ችግሮችን በጋራ መፍትሄ ለመሻት በመነሳት ያለመተማመንን ደረጃ በደረጃ ለመቅረፍ ይችሉ ዘንድ፡-

- ችግሮች መኖራቸዉን መቀበል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ ነጥብ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት በአመዛኙ ተበዳይ የሆነው ወይም ነኝ የሚለው ወገን የደረሰበትን እና መኖሩ እንድታወቅለት የምሻውን ችግር በዳይ ከችግር እንዳይቆጠር የምፈልግ አሊያም የማይቆጥረው በመሆኑ ፡፡
- ችግሮቹ የጋራ ስለ መሆናቸው መተማመን ላይ መድረስ መቻል ወሳኝነት ስለአለው በዚህ መስከ ቀጣይነት ያለው ብርቱ ስራ መስራት
- በጋራ ችግሮችን ለመፍታት ካልፋቀዱ ሁሉም በየፊናቸው የበለጠ ዋጋ እንደሚከፍሉ እንዲገነዘቡ ማስቻል
- **የማህበረሰቡ አባላት** ዛሬም ሆነ ከዚህ ቀደም በታሪክ ሂደት **ስ**ለችግሮች ስለመኖራቸው ከተማመኑ በኋላ ችግሮቹን የሚመጥን መፍትሄ ለመሻት መስራት
- በዋነኛ ችግሮች እና በአባባሽ ችግሮች መካከል ያለዉን ልዩነት ጠንቅቆ ማወቅ
- ችግሮች የሚነሱበትን ግዜ ድግግሞሻቸውን ለማወቅ መጣር
- የችግሮችን ቀስቃሾች ለይቶ ማወቅ፡- ከፋፍለው ለመግዛት የሚተጉ መሪዎች ወይንስ ስሜታቸዉን መቆጣጠር የተሳናቸው **የማህበረሰብ አባላት**
- በችግሮች ፍቺ እና ክብደት/ ጥልቀት ላይ የተቀራረበ ግንዛቤ ማስጨበጥ ማለትም ሚዛናዊ እና ባልተጋነነ መልክ ማቅረብ መቻል
- በችግሮች መባባስ ተጠቃሚ የሆኑ ሃይሎችን ለይቶ በማወቅ፡፡ ይህ ችግሩን ለማባባስ እንደሚያሴሩ ከታወቀ ማክሸፊያ ለማበጀት ይረዳል

ችግሮች የጋራ ስለ መሆናቸው መተማመን ላይ መድረስ መቻል፡፡ ይህ ችግሮችን በጋራ ጥረት ለመፍታት ካልፋቀዱ ሁሉም በየፊናቸው የበለጠ ዋጋ እንደሚከፍሉ ያለው ግንዛቤ በልቦናቸው ማስረፅ፡፡ በማስከተልም የመተማመን ግንባታ ፈር ለማስያዝ የሚከተሉትን ነጥቦች በጥሞና ማከናወን ይጠበቃል

- ለስኬታማ የወደፊት አብሮነት እያንዳንዱ አካል ከሌላው ጋር አጋርነት ለመፍጠር ምን በጎ አስተዋጽኦ እንደ ሚጠበቅበት ሃሳብ እንድያመነጭ እንዴትስ በስራ እንደ ሚተረጉመው እንዲያሳይ ማነሳሳት
- ከባላንጣነት ወይም ከተፎካካሪነት ወደ አጋርነት ሽግግር በምን ወቅት እንደሚቻል እንዴትስ እንደሚፋጠን የጋራ እቅድ እንዲነደፍ እና እንዲተገበር ማበረታታት
- ለስኬታማ የጋራ ኑሮ በፖለቲካ መስከ የሚፈጠረው ስምምነት በእያንዳንዱ ግለሰብ እና ማህበረሰብ ምን እይታ እንዳለው በመገምገም ተቀባይነት እንዲኖረው ለጋራ ስራ ማነቃቃት
- ለስኬታማ የጋራ ኑሮ በጋራ ስለመስራት ጥርጣሬ ያላቸዉን ወገኖች ለማሳመን በጋራ ምን ሊሰራ እንደሚገባው እቅድ ማውጣት

- በተሳካ መልኩ በጋራ ኑሮ  ልንኗኗር እንደማይቻል በማማመን አሻፈረኝ ያሉትን ግለሰቦች ሆነ ቡድኖች ስጋታቸዉን እንደሚካፈሉ በማስረዳት እና ግዜ በመስጠት  የማግባባት ስራ መሥራት
- አንዱ ስለሌላኛው ያለውን ጥያቄ /ብሶት ወዘተ የተሳሳተ ግንዛቤ ለማረም በሚል የጋራ ስራ መስራት እውነተኛ ስጋት ካለም ተግቶ በመስራት ማስወገድ
- የሚፈጠረዉን ለጋ ህብረት ለመንከባከብ በጋራ ምን ሊሰራ እንደሚገባ እቅድ ማውጣት
- የሚፈጠረዉን ለጋ ህብረት ሁሉም እነደ ማይቀበል ታውቆ እጅግ ከፋፋይ የሆኑ ርእሶችን ወደሁዋላ በማቆየት በመልካም ገጽታዎች ላይ እርምጃን መጀመር
- በግለሰብ ደረጃም የሰዎች ግንኙነት ከቀድሞ ታሳቢ ባላንጣ ጋር በየደረጃ ግንኙነት መፍጠርን እንዲማሩ ማነሳሳት ለዚህ ደግሞ የአካባቢ ማህበራት ( local association and communities ) ትልቁን ድርሻ እንዲይዙ ማድረግ
- አስፈላጊ ሲሆን  የማይመቹ ዉሎችን መቀበል ዕንዳለ ማወቅ

2. <u>ፍትሀዊ  እና  በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ዘላቂ  ዓንድነትን ለመገንባት  የሚያስችል</u>

- ያለመተማመን  ችግር  ስለ መኖሩ ስምምነት  ላይ ከተደረሰ  ችግሩን በፖለቲካ መስከ ለመቅረፍ
- *መንስኤዎቹ ወይንም ምክኒያቶቹ መታወቅ ይኖርባቸዋል*
- ላለመተማመናችን  አንዱ እና  ዋነኛው  ምክንያት የእኛ ኢትዮጵያን በሃገራችን ኢትዮጵያ የእኩል ባለቤትነት መብት ያለን መሆናችንን ከልብ ለመቀበል ዝግጁ ያለመሆችን  ነው

ለመሆኑ በሃገራችን ኢትዮጵያ የእኩል ባለቤትነት መብት ወይም ስሜት ያለን መሆናችንን የመቀበል ችግር በእኛ በኢትዮጵያን መካከል አለን ?

- ሃሳቡን ስትቃወም      <u>ኢትዮጵያዊ አይደለህም</u>
- የሌላኛዉን ብሶት/ ጥያቄ በጥሪጣሬ የማየት መብት ለራሱ መስጠት
- የሌላኛዉን ታሪክ ማስተባበል
- የሌላኛዉን እምነት መጤ አድርጎ  የራሱን ከዛው የፈለቀ በማስመሰል መውሰድ

ካለስ ለምን በግልጽ በሃገራችን ኢትዮጵያ የእኩል ባለቤትነት መብት  የለንም  የምንል አንሰማም ?

- በህግ የሚያስጠይቅ በመሆኑ በገሃድ አንለውም

- የብቸኛ የባለንቤትነት ማስረገጫ ሃረግ ወይም ዓረፍተ ነገር በ 21 ኛው ክፍለ ዘመን በሞራል ደረጃ የሚያሳፍር በመሆኑ

ይ ህ አዲስ ክስተት ነውን ካልሆነስ በዘመናችን ለምን ጎላ ብሎ ይሰማል ?

- ባለንበት ዘመን በበርካታ የአለማችን ክፍሎች እንደ ተከሰተው የሃገራችን ህዝቦች ስለሙብት ያላቸው ግንዛቤ በመለወጡ ሳቢያ ዜጎች በሃገራቸው የእኩል ባለበትነት መብታቸው በሁሉም መስክ እንዲጠበቅ መጠየቅ መጀመራቸው

በአሁኑ ግዜ ጉዳዩ ጎላ ብሎ መሰማት መጀመሩ ምንን አስከትሎዋል

- አሰርትቭ መሆን ስጋት ፍጥጫ
- **ካለ ምክኒያቱ ምን ድነው**

በሃገራችን ለዘመናት ተንሰራፍቶ የነበረው የተዛባ ስርአት አስከትሎት የነበረው ሚዛን የሳተ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ስርአት ለረዥም ዘመናት የሃገርን አመራር ከአንዱ የህዝባችን አካል የወጡ ልሂቃን በሞኖፖል በመያዝ፡-

- በብቸኝነት የሃገር ባለቤትነትን እንዲሞግቱ
- እራሳቸውን ብቸኛ የሃገር ተቆርቋሪ አድርገው እንዲያቀርቡ መፍቅዱ
- ለሌላኛዉ ወገን የመገለል ስሜት እንዲሰማው ማድረጉ
- በሙሉ መንፈሰ ለአንድነት ከመቆም እንዲያፈፍግ ማድረጉ

ለዘመናት ተገልለሎ ከነበሩ ህዝቦች አብራክ የወጡ ሊሂቃን እና የማህበረሰብ አባላት በሃገራችን ኢትዮጵያ የጋራ ባለቤትነት መብት መጠየቅ መጀመር በታሪክ አጋጣሚ የሃገርን አመራር በብቸኝነት ይዘው የነበሩትን ጥቅም በቀጥታ ስለሚገታ ይህ ጉዳይ ለአንዳንድ ልሂቃን ባለመመቸቱ ያለመተማመን ሰፍኖ ሁለም ወገን ለጋራ ጥቅም በጋራ ከመቆም ይልቅ መጠላለፍ ለመምረጥ መገፋፋቱ ነው

የሃገራችን የተዛባ ታሪክ የአንዱን ህዝባችንን እምነት ማለትም ክርስትናን እንደ ሃገር በቀል እስልምናን እና የአይሁድ ወይንም ቤተ ፈላሻ መጤ አድርጎ በማቅረቡ እና በዚህ እይታ ዙሪያ ለረዥም ዘመናት የተቀናበረ ስራ በመሰራቱ ታሪክን በጥልቀት ለማየት ብቃት የሌላቸዉ ወገኖቻችን እይታዉን ብቸኛ እዉነት አድርገው በመውሰድ ሌሎች ወገኖቻቸዉን እንደመጤ መቁጠራቸዉን የሚያሳይ አመላካች ድርጊቶች ማሳየታቸው

በተዛባው አመራር እና ውጤቱ በሆነው የተዛባ ታሪክ ተጠቃሚ የሆኑት ልሂቃን በ 21 ኛው ክፍለ ዘመን ብቸኛ የሃገር ባለቤትነትን ስፍራ ይገባኛል በማለት እና በይፋ መፋለም ህሳቤው ቀጣይነት እንዲኖረው በግልጽ መፋለም። ምንም እንኳ በግልጽ መናገር አሳፋሪ ቢሆንም በተዘዋዋሪ ይህን ህሳቤ ማንጸባረቅ እና ማራመድ ስለሚታይ የሶስቱ እምነት ተከታዮች በሙሉ ልብ ለመቀራረብ ግዜ ወስዶባቸዋል ዛሬም ፈተናዉ ቀጣይ ሆኗል

በዘመናችን የዲሞራሲ ጭላንጭል መታየት እና የመገናኛ ብዙሃን መስፋፋት ምክንያት ዜጎች ስለ ማንነታቸዉ assertive አሰርትቭ መሆን እንደ ጽንፈኛ እንዲቆጠሩ አድርጓል

- ተገልለው የነበሩ ህብረተሰባችን ክፍሎች ራስን በራስ የማስተዳደር እና በሃገር የጋራ ባለቤትነት መብት መጠየቅ
- Previllged የነበረው ያለዉን የማጣት ስጋት
- ከአንዱ የህዝባችን አካል የወጡ ሊሂቃን የሌሎች ተመሰሳይ

**መቀራረብ ይጀመር ዘንድ**

ያለመተማመን እየጎላ በመጣበት ህብረተሰብ ውስጥ ግለሰቦች ሃሳብን መለዋወጥ እና የተለያዩ ሃሳቦችን ከማንሸራሸር መታቀብ ብቻ ሳይሆን የሚርቁት በአካልም ነው። በተወሰኑ ስፍራዎች ላይ በጋራ ላለመገኘት መወሰናቸውን ተከትሎ የአካል እና የስነ-ልቦና መራራቅም እንዲሁ እየጎላ ይመጣል።

ይህ ስር የሰደደ የማህበረሰብ ያለመተማመን ወደ መፍትሄ ሊያመራ የሚችለው ከሁለቱም የማህበረሰብ ክፍልሎች የመጡ ውጤት ተኮር አካሎች በጋራ ሲሰሩ ነው። ባለመተማመናቸው በማህበረሰባቸው ላይ የደረሰውን በደል እና አደጋ በጥሞና በመመርመር መስዋዕት ለመሆን እና ህዝባቸውን ለማቀራረብ ያለሰለሰ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል። ሰዎች ልዩነታቸውን እንዲያጠቡ ከሚገፋፏቸው ነገሮች መካከል በአምባገነኖች የሚወሰዱ እጅግ አሰቃቂ እና መረን ያለፈ የጭካኔ እርምጃ ነው። በዚህም ተራርቀ የነበሩ ግለሰቦች በመሃከላቸው ሰፍሮ የነበረን ያለመተማመን ለመቀነስ በጋራ እንዲሰሩ ያበረታታል ።

እንግዲህ ከነኝህን ሁለት አጋጣሚዎች በመጠቀም ማለትም ክፉ አጋጣሚዎች በመጡ ግዜ ለዛ አፀፋ ለመጣደፍ ሳይሆን የረዥም ግዜ እቅድ አውጥቶ ያንን እንዴት ለዘላቂ መፍትሄ በዘላቂነት መጠቀም እንደሚቻል ዕቅድ ማውጣት ነው። ከዛም በተጨማሪ ይህ ወደ አንድነት የመምጣት እና ያለመተማመንን የማስወገድ concious መሆን የተከሰተበትን ሁኔታ ተከትሎ በጋራ ለማንቀሳቀስ የሚቻልበትን እቅድ መንደፍ ነው። ለዚህ ዋንኛው መሰረቱ motivated የሆኑ ከሁለቱም የህብረተሰብ ክፍሎች የተነሱ አካላት ችግሩ መኖሩን በትክክል መቀበላቸው ነው። የመጀመርያው የችግሩን መኖር መቀበል እና ለችግሩ እውቅና መስጠት ነው። ይህን ካደረጉ እሱን ተከትሎ የችግሮችን ቅደምተከተል በማስፈር የትኛውን ችግር ቀድሞ መፍታት መፍትሄው ሊፋጠን እንደሚችል ወይም በርካታ ደጋፊዎች ሊኖሯቸው እንደሚችሉ ጥናት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

እንግዲህ አንድ ማህበረሰብ የዚህ አይነት ስር የሰደደ ያለመተማመን ችግር ያለበት መሆኑ ከታወቀ የተለያዩ ተቋማት ይሁኑ ግለሰቦች ለችግሩ እልባት ለማግኘት ሲባል የሚጫወቱት ሚና ይኖራል። ይህንንም በተመለከተ ከዚህ በታች የተቋማት እና የግለሰቦችን ድርሻ ለመዳሰስ እንሞክራለን።

በግለሰብ ደረጃ ሰዎች ሊጫወቱት የሚገባ ሚና

የመገናኛ ብዙሃን ሊጫወቱት የሚገባ ሚና

የትምህርት ተቋማት ሊጫወቱት የሚገባ ሚና

ክፍል ሶስት

ያለመተማመን ለመቅረፍ በግለሰቦች ደረጃ ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች፡- በቅድምያ ስር የሰደደ ያለመተማመን ያለበትን ህብረተሰብ ለማቀራረብ የሚደረገው ስራ የሚጠይቀው ትዕግስት ከፍተኛ መሆኑ ታውቆ በቂ ዝግጅት ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው።

- ውጤት ለማየት ያለመጣደፍ
- በየደረጃው ማዳለጥ እንዳለ እና ወደፊት ከተኬደ ቡሃላ ማፈግፈግ እንዳለ ተገንዝቦ በትዕግስት እና በፅናት ችግሮችን በየደረጃቸው ለመቅረፍ መሞከር እጅግ አስፈላጊ በመሆኑን እያንዳንዱ ወገን አምኖ ሊቀበል ይገባል።

በግለሰብ ደረጃ በመጀመርያ የሚጠበቀው ችግሩ መኖሩን በትክክል ማመን ነው። አንድ ግለሰብ ሆነ ብዙ ግለሰቦች ችግር መኖሩን ካላመነ/ኑ ወደ መፍትሄ ሊራመድ አይችልም። ስለዚህ ማህበረሰብን ያራራቁ አንዱ ሌላኛውን እንዲጠረጥር ያደረጉ ችግሮች ስለመኖራቸው ማወቅ እና ለዛ መፍትሄ ለመሻት ዝግጁነትን ማሳየት ያስፈልጋል። ለችግሮች እውቅና ከተሰጠ ቡሃላ ችግር ተብለው የሚታሰቡትን ከተለያዩ ማዕዘናት ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አራርቀውናል ብለው ያሰቧቸውን ችግሮች እንዲያሰፍሯቸው ማበረታታት። በማስከተል በግልፅነት እና አድሎ በሌለበት መልኩ ችግሮች ከሁሉም አቅጣጫ ሁሉም ወገን በዝርዝር እያንዳንዱ ችግር ላይ ለመነጋገር ብቃት የሚኖርበትን ሁኔታ ማመቻቸት።

በሶስተኛ ደረጃ በወጡት ዝርዝር የችግር አይነቶች ቅደም ተከተል ላይ ለመነጋገር ይቻል ዘንድ ዓላማን ግልፅ ማድረግ ነው። ይህም የሚደረጉ ውይይቶች እና የሚደረጉ ስብሰቦች ሁላ ውጤት ተኮር መሆናቸው እና መፍትሄ ለማምጣት እንጂ ችግር ለማባባስ እንዳልሆነ ማሳወቅ። ሁሉም ወገን ውይይቶችን በሚጀምርበት ግዜ የሚያነጣጥረው መፍትሄ ላይ እንዲሆን መመካከር እና መተማመን ደረጃ ላይ መድረስ ያስፈልጋል። ይህ የሚያስፈልግበት ዋናው ምክንያት ጣት መቀሳሰርን ለማቆም እና አንዱ ሌላኛውን ለመርታት የሚመጣበትን የሽንፈት እና የኪሳራን ጉዞ ለማስቀረት ይረዳል። ይህ ካልታረመ ዳግም ለመመለስ አስቸጋሪ ወደሚሆንበት ችግርን የማክረር እና የመረራራቅ ደረጃ ስለሚያመራ ሁሉም ወገን በጥሞና ሊያስብበት ይገባል።

ስለሆነም ወደ ውይይት መድረኮች ስንመጣ ለማሸነፍ ሳይሆን መፍትሄ ለመፈለግ መሆን እንዳለበት ሁላችንም በልቦናችን ልናሰርፀው ይገባል። ውይይቶች ስኬታማ ይሆኑ ዘንድ ቀለል ካሉ ችግሮች መጀመር አስፈላጊ ነው። ብዙ ወገኖች ሊፈቱ ይችላልሉ ብለው ሚያስቡዋቸው እና የሚስማሙባቸው ችግሮች ላይ በቅድምያ በመነጋገር ደረጃ በደረጃ መተማመን እየሰፋ ስር እየሰደደ እንዲመጣ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ቀለል ያሉትን ችግሮች መፍታት ከተቻለ በሂደት ወደ አስቸጋሪ እና አሻሚ ወደሆኑ አነታራኪ ጉዳዮች ማምራት ይቻላል። ነገርግን እጅግ አወዛጋቢ ከሆኑ ችግሮች መጀመር ለሚደረገው ጥረት ውድቀት ስለ ለሚያስከትል ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል። ባየነው እና በልምዳችን ብዙውን ግዜ ውይይቶች የሚጀመሩት እጅግ አስቸጋሪ ከሆኑት ርእሶች ስለሆነ ብዙም እርምጃ ሳንራመድ መፈረካከስ መጥቶ እንደገና ላንገናኝ ተረጋግመን የተለያየንባቸው አጋጣሚዎች በብዛት ስላሉ ወደዛ ላለመግባት ጥንቃቄ ልናደርግ ይጠበቅብናል።

ውይይቶችን የተቃኑ ለማድረግ የመተማመን አስፈላጊነት በተለያዩ ፀሃፊያን እና ቀና አሳቢዎች ዙርያው ፅሁፎች እየተበተኑ የመነጋገርያ ርእሶች እንዲሆኑ ማድረግ ሌላው የግለሰቦች ሃላፍትና ነው። ስኬታማ የሆኑ የውይይት ስልቶች ፣የመነጋገር እና መቀራረብ ዘዴዎች ምን እንደሆኑ አንዱ ለሌላው ልምድ እንዲያካፍል የሚረዱ ስነ-ፅሁፎች በብዛት እንዲበተኑ እገዛ ማድረግ የዜጎች ሃላፊነት ስለሆነ በዛ መስከ ማበርታት አስፈላጊ ነው። ውይይቱ ቀጣይነት ያለው በሆነ መንገድ እና ለጠላት ቀዳዳ በማይከፍት

መንገድ ሆኖ መጓዝን ይፈልጋል። የሶሻል ሚዲያው ሆነ በተለያዩ መድረኮች የሚጻፉም ፅሁፎች ሆነ ተጋብዘው የሚመጡ ግለሰቦች targeted የሆኑ ስራዎችን ብቻ እንዲያቀርቡ ማበረታታት። ለእርቅ ፣ ለመስማማት እና ለመቀራረብ የሚያስችሉ ብሎም የመራራቅን ነቀርሳ ለመንቀል የሚያስችሉ መፍትሄዎችን የሚያቀርቡ ሃሳቦች ላይ ትኩረት ያደረጉ ስነ-ፅሁፎች እና ውይይቶች ላይ እንዲያተኩሩ ማበረታታት እና ወይይቶችን መምራት አስፈላጊ ነው ።

ተጋብዘው ወደ ውይይት መድረኮች የሚመጡ ግለሰቦችም በቀና መንፈስ የመቀራረብ መንፈስን ሊያመጡ የሚችሉ እንዲሆኑ ተደርጎ poleraised የሆኑ ግለሰቦችን በማግለል ለመከፋፈል የሚመጡን ድምፆች በመነጠል ላይ ጥረት ሊደረግ ይገባል። ነገር ግን በዚህ አይነት ጉዞ ውስጥ ከፋፋይ የሆኑ ግለሰቦችን በመጋበዝ እና መድረኮችን ለንትርክ እና ለውዝግብ ክፍት የማድረጉ ሁኔታ የማያዋጣ ስለሆነ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል። ከዚህ በተጨማሪ ጉዳዩን ወደ ማህበረሰባችን እንዲወርድ ከተፈለገ እና ውጤታማ ይሆን ዘንድ አክቲቪስቶች ፣ ጦማርያን በድህረ-ገፆቻቸው እና በተለያዩ ስፍራዎች በሚቀርቡበትም ግዜ ትኩረታቸ ለመስማማት እና ጥርጣሬን ለማስወገድ በሚል ርእስ ላይ ያተኮረ ቢሆን የተመረጠ ይሆናል። የሃይማኖት አባቶችም በፀሎት ስፍራዎች ለምእመናን ይህን መልእክት ቢያስተላልፉ እና የስብከታቸ ትኩረት ጥርጣሬን ማስወገድ እና በአንድነት ከሌሎች እምነቶች ጋር በጋራ የመኖር ጉዳይ በሃይማኖትም የተወደደ ስለመሆኑ የማስተማራቸው ሁኔታ በተግባር ወደ ማህበረሰብ የወረደ ስራ ለመስራት ያግዛል።

በተጨማሪም የውይይት መድረኮች በተከታታይ ዘላቂ የሆነ የመተማመን መንፈስ ለማስፈን የሚቻልበትን የውይይት አካሄድ መምረጥ። ግለሰቦችም ቀና አስተሳሰብ ላይ በማተኮር ውጤት የሚያስገኙ ውይይቶች እንዲያደርጉ targeted የሆነ ውይይት ማድረጉ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። የህብረተሰቡን መቀራረብ የማይፈልጉ አካላት የሚያደርጉትን ደባ ለማክሸፍ ይቻል ዘንድ የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶች ዝርዝር ለህዝብ ግልፅ ማድረግ። በዚህም ሰዎች ነቅተው እንዲጠባበቁ ማድረግ። መቀራረቡን የማይፈልጉ ሰዎች ምን አይነት መንገዶች እና ዘዴዎች ከፋፋዮች እንደሚጠቀሙ በመግለፅ ንቁ የሆነ ጥበቃ ተደርጎ በዚህ አይነት የተሰማሩ ግለሰቦችን ማግለል አስፈላጊ ነው። ከዛም በተጨማሪ የከፋፋዮችን ሴራ ለይተው የሚያወጡ ንቁ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በተቀነባበረ መንገድ መረጃ እየተቀባበሉ በዚህ የተሰማሩ ሰዎችን ማጋለጥ እና ከጥፋታቸው እንዲታቀሙ ማስተማር እና መምከር ተገቢ ሆኖ ይገኛል።

እንግዲህ ከላይ ከተዘረዘሩት መረጃዎች መረዳት የምንችለው ከዚህ ቀደም የተጓዝንበት የጉዞ መስመር የማያዋጣ መሆኑን ተገንዝበናል። ማለትም ከፋፋዮች ከፋፈሉን ፣ መንግስት አንድነታችንን ስለማይፈልግ ከፋፍሎን ነው የሚለውን በሶስተኛ ወገን ላይ ያነጣጠረን እርግማን ማውረድ መተው። ከዛ በተጨማሪ ችግሩ ከኛም ጭምር መሆኑን ተገንዝበን በኛ በኩል እርምት አድርገን ላለመከፋፈል ወስነን በዚህ ላይ መስራቱ እጅግ ወሳኝነት ያለው ነው። ነገር ግን ተመልሰን ችግሩን ወደ ሌላኛው አካል ላይ በማዘዋወር ስለከፋፈሉን ተከፋፈልን የሚለው ተራ ምክንያት ስር መደበቅ መሞከር ታጥቦ ጭቃ ስለሆነ ከዛ ተጠብቀን እየተመካከርን ወደፊት መሄድ ነው። እንግዲህ መተማመን ይፀና ዘንድ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦች ሰጥቶ መቀበልን መማር ነው። አንዱ ወገን ቀና መንገድ ባሳየ ግዜ ያን ቀና መንገድ ተከትሎ ቀና መንገድ ማሳየት ቀንእርምጃ ነው።

ክፍል 4

በግለሰብ ደረጃ የሚጠቀሰው ቀዳማዊ ችግር ሌላኛው አካል በክፉ ላይ ባነጣጠረው መልኩ መረጃዎችን በማሰባሰብ መሰረተቢስ የሆኑ ጥላቻዎችን እና ፍራቻን እንዲደላደል ያደረጉ ክፍሎች ይህን ችግር በግልፅ ለመቅረፍ ዝግጁነታቸውን ማረጋገጥ እና ለዛ ስራ መጀመርን ማሳየታቸው ነው። በመሆኑም

ይህንን ችግር ለመቅረፍ አካላዊ መቀራረብ እና መተዋወቅ አስፈላጊ ስለሆነ የመቀራረብን እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁነትን ማሳየት ከግለሰቦች የሚጠበቅ ነው፡፡ በአካል መቀራረባቸውም ከዚህ ቀደም ይሰሙት የነበረውን የተዛባ ሃሳብ ስህተተኛ መሆኑን በመገንዘብ እውነተኛ የሆኑ መረጃዎችን አሰባስበው በልበሙሉነት ከወገናቸው ጋር እንዲሰሩ የሚያበረታታቸው ሲሆን ይህ አካላዊ መቀራረብ እጅግ ወሳኝነት ያለው ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን ሊስተዋል የሚገባው ይህ አይነት አካሄድ ለረዥም ግዜ የተደላደለ ያለመተማመን ባለበት ህብረተሰብ ውስጥ በቀላሉ ወደ ግብ መድረስ የማይቻል ስለሆነ ግለሰቦች ይህንን በማወቅ በትዕግስትና በፅናት ስራቸውን ለማከናወን ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሌላኛው ነጥብ በሁለቱም ወገን የሚገኙ ግለሰቦች ያለመተማመንን ለማስወገድ በትጋት ለማስወገድ እንደቆረጡ በግልፅ ማሳወቅ እና ቃል-ኪዳን መግባታቸው engaged እንዲሆኑ የሚገፋፋቸው እና ለክብራቸው ሲሉ ይህንን ሃላፊነት እንዲረከቡ የሚያበረታታቸው ስለሆነ በዚህ ስራ እንዲገፉበት ይጠበቃል፡፡ በመቀጠልም ከአንድ ወገንም እንኳ በተገባው ቃልኪዳን መሰረት ቀዳሚ እርምጃ በመውሰድ ከቃል-ኪዳኑ ጋር የሚጣጣም ድርጊትን መፈፀም መጠራጠርን የሚቀርፍ ስራ ሰርቶ ማሳየት ሌላኛው ወገን እንዲቀላቀል ስለሚያበረታታ በቀደምትነት እርምጃ የወሰደው እና የእርቅን ጎዳና የወሰደው አካል በፅናት ከሌላኛው አካል ብዙም ሳይጠብቅ በበጎ ድርጊቱ ቃሉ እና ድርጊቱ ተመጋገበው ተደጋግፈው ማሳየቱ ሌላው የሱን አርአያ እንዲከተል ሊያበረታታው ይችል ይሆናል፡፡

በቀዳሚነት ወደመተማመን እርምጃ ለመሄድ የወሰደው አካል የአፀፋ ምላሽ ወዲያውኑ እንኳ ባያገኝ በጥንቃቄ በበጎ ስራው መግፋት መቻሉ ሌላኛው ጥርጣሬው የከፋበት ወገኑ ተበራቶ መልካሙን ጎዳና እንዲቀላቀል እና ያለመተማመንን በጋራ ተጋግዞ እንዲቀርፉ የሚያስችል ስለሆነ ትዕግስት እና ፅናት ይጠበቃል፡፡ ይህ አይነት የበጎ አርአያነት ስራ መተማመንን ለመገንባት መሰረት ስለሆነ እያንዳንዱ ወገን ይህንን ሃላፊነት ለመወጣት ቃል በገባው መሰረት engagment መፈፀም ይጠበቅበታል፡፡

የቃልኪዳን እና የድርጊት መጣጣም የግለሰቦች በተጠበቁበት መገኘት ሌላኛው ተጠራጣሪ ወገን ቢኖር እንኳን መልካም የአፀፋ ምላሽ እንዲሰጥ ያነሳሳዋል፡፡ በቀና መንገድ የመተማመንን ግንባታ ማለትም confidence building ላይ በቀዳሚነት የሰራው ወገን አፀፋዊ ምላሽ አርአያ የሆነው አካል ሌላኛው አካል እንዳይበለጥበት እና ብልጠት አገኘሁ ብሎ ያየተፈጠረችውን ግኙነት እንዳያደፈርስ ግንኙነቱ ከተቃረጠ የሚያጣው ነገር ከዛ የላቀ መሆኑን በማሳወቅ ወደ ብልጠት የሚያደላውን ወገን ለጥቅሙ ስሊ እንኳን የመጠራጠ rn መንፈስ እንዲቀርፍ እና ወደ አንድነት እንዲመጣ ጥረት ማድረግ ማበረታታት እርምጃዎችን ማጠንከር ይችላል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ መንገድ ቁልፍ የሆነው የአሰራር ስልት ሰቶ መቀበልን መርህ እንደ መሰረታዊ የመተማመን መገንብያ መቀበል እና ለመቀበል ተግቶ መስራት ነው፡፡ አፀፋ ለመስጠት መቀበልን ልምድ ማድረግ የጎዶሎ ነጥቦችን ስጦታ በመቀባበል የተቀበለው መስዋትነት መልሶ ለሌላኛው ወገኑ ተመሳሳይ ካሳ መክፈል ተአማኒነትን የሚያጎለብት ስለሆነ ሰቶ መቀበልን የግንኙነቱ መሰረት አድርጎ በፅናት መግፋት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ አይነት አሰራር ከባህል ጋር ሊጋጭ ስለሚችል እና ሰዎች ስለሰጠህ እንዲከፈልህ ፈለክ የሚለውን መጥፎ የባህል ጉዞ ለዚህ መጥፎ እንቅፋት ሊሆን ስለሚችል እንዲህ አይነቱን የባህል እንቅፋት ወደ ጎን በመተው ሰቶ መቀበል መሰረታዊ የመተማመን ግንባታ confidence building ገፅታ መሆኑን ተቀብሎ በዚህ በፅናት መግፋት ይጠበቃል፡፡ ሰጥቶ የመቀበል ልምድ ለተሰጠው ነገር ምላሽ መስጠት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በጋራ ለመስራት ትብብርን ለማዳበር ፋይዳ እንዳለው ጥርጥር የለውም ነገር ግን ግለሰቦች ተቀብሎ መስጠትን ልምድ ስለሚያደርጉ ቀድሞ ሰጥቶ በበጎ ልገሳ የመግፋትን አርአያነት ቸላ እንዲሉ ስለሚያደርግ ሌላ እንቅፋትነት ሊኖረው ይችላል፡፡

ይህም ማለት ሰጥቶ መቀበል ከሆነ እና አንደኛ አፀፋ እስካልመለሰ ድረስ መጠበቅ ስለሌለበት በአርአያነት ለመመደብ መስጠትን መቀጠል የሚለውን የመፍትሄ ሃሳብ ስለሚቃረን ይህ ጥንቃቄ የተሞላበት ጉዞ መጠራጠ rn ደረጃ በደረጃ ሊቀርፍ ስለሚችል እንደሌላ አማራጭ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

## 3. <u>ፍትሀዊ እና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ዘላቂ ዓንድነትን ለመገንባት የሚያስችሉ እርምጃዎች</u>

ያለመተማመን ችግር ስለ መኖሩ ስምምነት ላይ ከተደረሰ ችግሩን በፖለቲካ መስክ ብሎም በማህበረሰብ ደረጃ መቅረፍ ይቻል ዘንድ

- መንስኤዎቹ ወይንም ምክኒያቶቹን ማወቅ አስፈላጊ ነው። ላለመተማመናችን አንዱ እና ዋነኛው ምክንያት እኛ ኢትዮጵያን በሃገራችን የእኩል ባለቤትነት መብትን በተመለከተ የተስተካከለ ግንዛቤ ማጣታችን ነው።

ለመሆኑ በሃገራችን ኢትዮጵያ የእኩል ባለቤትነት መብት ወይም ስሜት ያለን መሆናችንን የመቀበል ችግር በእኛ በኢትዮጵያን መካከል አለን ? ይህ ስሜት አለ የሚሉ ወገኖች ከሚያቀርቧቸው የመከራከርያ ነጥቦች መሃከል እንደምሳሌ ልጠቀስ የምችለው ነጥብ፦ ቀደም ሲል በነበረው የተዛባ የአገዛዝ ስርዓት ተጠቃሚ ከነበሩ ከአማራ ብሄረሰብ የወጡ ልሂቃን መካከል የበላይነቱን ስሜት ቀጣይነት የሚሹ ክፍሎች እና ተከታዮቻቸው፦

- ስለሃገራችን ኢትዮጵያ እነሱ ካስቀመጡት የኢትዮጵያዊነት መስፈርት ውጭ የተለየ ሃሳብ በሚነሳበት ግዜ <u>ኢትዮጵያዊ አይደለህም</u> የሚል አግላይ ባህርያት ማንፀባረቃቸው
- የሌላኛዉን ብሶት እና ጥያቄ በጥርጣሬ የማየት መብት ለራሳቸው መስጠታቸው
- ሌላኛው ስለሃገራችን ኢትዮጵያ ያለውን የተለየ እይታ ለሃገር ደህንነት ስጋት አድርጎ ማቅረብ
- የሌላኛዉን ታሪክ ማስተባበል እና የኔ ሚሉትን በተቃራኒው ማጉላት ብሎም ብቸኛ እውነት አድርጎ ማቅረብ
- የብሄር ብሄረሰብን ማንነት ወይም የራስ መገለጫ የሆነን ቋንቋን ማስተባበል እና ሌላው ስለብሄሩ ያለውን ግንዛቤ ለሃገር መከፋፈል ምክንያት አድርጎ ማቅረብ ወዘተ በሚል ያስቀምጧቸዋል

በሃገራችን ኢትዮጵያ ለምን በግልጽ የእኩል ባለቤትነት መብት የለንም የምል ግለሰብም ሆነ ቡድን አንሰማም? ለዝህ ምክኒያቱ

- የብቸኛ የባለንቤትነት መብት መሞገት በ 21 ኛው ክፍለ ዘመን በሞራል ደረጃ የሚያሳፍር በመሆኑ በፖለቲካዊ እይታ ተቀባይነት የለለው መሆኑ
- በህግ ከሚያስጠይቁ ጉዳዮችም በመሆኑ በገሃድ ለማለት አያስደፍርም

አገርን አስመልክቶ  የእኩል ባለቤትነት መብት መሞገት አዲስ ክስተት ነውን?   ካልሆነስ በዘመናችን ለምን ጎላ ብሎ ይሰማል ?

በአገር ላይ የእኩል ባለቤትነት መብትን መሞገት ቀደም ሲልም እጅግ ዝቅተኛ በሆነ መልክ የነበረ ቢሆንም ባለንበት ዘመን በበርካታ የአለማችን ክፍሎች እንደ ተከሰተው የሃገራችን ህዝቦች ስለመብት ያላቸው ግንዛቤ በመለወጡ ሳቢያ ዜጎች በሃገራቸው የእኩል ባለበትነት መብታቸው በሁሉም መስክ እንዲከበር መጠየቅ መጀመራቸው ተስተውሏል። ስለዝህ ይህን በዘመናችን ዜጎች እንድሚላላቸው የምሹትን መብት ለመረዳት እና ለማክበር መሞከር በሰላም ለመኗናር የተሻለ አጋጣሚ ይፈጥራል።

<u>በአሁኑ ግዜ ጉዳዩ ጎላ ብሎ መሰማት መጀመሩ ምንን አስከትሎዋል?</u>

- ለመብት መቆርቆርን በተመለከተ በአለማችን ዙሪያ ከታየው ለውጥ ጋር በተያያዜ  ሁኔታ የዘጎች በልበ ሙሉነት ማንነትን ለማስከበር መንቀሳቀስ ይታያል። የዝህም አንገትን ደፍቶ ከመኖር በልበ ሙሉነት ማንነትን ለማስከበር ወደ መንቀሳቀስ የታየው ለዉጥ አሰርትቨ መሆንን ስላጎላ በአንዳንድ የማህበረሰባችን አባላት      እንደ ፍጥጫ ተቆጥሮ ስጋት ፈጥሮ ታይቷል

<u>የዘጎች  በልበ ሙሉነት ማንነትን ለማስከበር መንቀሳቀስን እንደ ስጋት ምንጭ የመቁጠር **ስሜት ምንጩ ወይንም ምክኒያቱ ምን ድነው?**</u>

በሃገራችን ለዘመናት ተንሰራፍቶ የነበረው የተዛባ ስርአት አስከትሎት የነበረው ሚዛን የሳተ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ስርአት ለረዥም ዘመናት የሃገርን አመራር  ከአንዱ የህዝባችን አካል የወጡ ጥቂት ልሂቃን እና የጥቅም ተጋሪዎቻቸው  በሞኖፖል እንድይዙ በማድረጉ በዝህ ዘርፍ የምመደቡ የማህበረሰባችን ክፍሎች፡-

- በብቸኝነት የሃገር ባለቤትነትን እንዲሞግቱ
- እራሳቸውን  ብቸኛ የሃገር ተቆርቋሪ አድርገው እንዲያቀርቡ መፍቀዱ እና  የጥቂቶች ብቸኛ የሃገር አዳኝ አድርጎ ራሳቸውን መመደብ  ለሌላኛዉ ወገን የመገለል ስሜት እንዲሰማው ማድረጉ ለመቀራረብ ጋረጣ ፈጥሮ ቆይቷል

በዘመናችን በአለም ዙሪያ በተፈጠረው መነቃቃት ለዘመናት ተገልለሎ ከነበሩ ህዝቦች አብራክ የወጡ ሊሂቃን እና የማህበረሰብ አባላት በሃገራችን ኢትዮጵያ የጋራ ባለቤትነት መብት መጠየቅ መጀመር በታሪክ አጋጣሚ የሃገርን አመራር  በብቸኝነት ይዘው ከነበሩት ጥቂቶቹ የእኩልነት ጥያቄን የእነሱን ስፍራ ስለምጋፋት የምደረግ አድርገው በመውሰዳቸው ያለመተማመን ሰፍኖ ሁለም ወገኖች ለጋራ ጥቅም በጋራ ከመቆም ይልቅ መጠላለፍ እንድበረታ  በማድረጋቸው ልዩነቶች እየሰፉ ለመሄድ በቅተዋል

የሃገራችን የተዛባ ታሪክ የአንዱን ህዝባችንን እምነት ማለትም ክርስትናን እንደ ሃገር በቀል እስልምናን እና የአይሁድ ወይንም ቤተ ፈላሻ  መጤ አድርጎ በማቅረቡ እና በዚህ እይታ ዙሪያ ለረዥም ዘመናት የተቀናበረ ስራ በመሰራቱ ታሪክን በጥልቀት ለማየት ብቃት የሌላቸዉ ወገኖቻችን እይታዉን ብቸኛ እዉነት አድርገው በመውሰድ ሌሎች ወገኖቻቸዉን እንደመጤ መቁጠራቸዉን የሚያሳይ አመላካች ድርጊቶች ማሳየታቸው

በዘመናችን የዲሞራሲ ጭላንጭል መታየት እና  የህዝብም  እንደ ጽንፈኛ እንዲቆጠሩ አድርጓል ባችን መብቱ

በዘመናችን የዲሞራሲ ጭላንጭል መታየት እና በመገናኛ ብዙሃን መስፋፋት  ምክንያት ዜጎች ስለ ማንነታቸዉ assertive መሆናቸው እንደ ጽንፈኛ እንዲቆጠሩ አድርጓል፡፡  ለምሳሌ ብንወስድ፡-

- ተገልለው የነበሩ ህብረተሰብ ክፍሎች ራስን በራስ የማስተዳደር ፣ በቋንቋ የመዳኘት፣ መማር ወዘተ እና በሃገር የጋራ ባለቤትነት መብት መጠየቅ መጀመራቸው እንደ ብሄርተኝነት መታየቱ
- በእምነቱ ምክንያት ተገሎ የነበሩት የማህበረሰብ ክፍሎች ዘመናችን በፈጠረው የ መረጃ መቀያየር መንልበት የፈጠረላቸውን አጋጣሚ በመጠቀም እምነታቸዉን ለማስፋፋት መቻላቸው እና በተለይም የተማሩ ወጣቶች ለማፍራቱ በመብቃታቸው  እምነቱን መተግበር ብሎም በግልፅ  manifest ማድረጉ  ያለመቻቻል መንፈስ እና አክራሪነት ተደርጎ  በሚሉ ፍረጃዎች ውስጥ መግባቱ
- Previllged የነበረው የህብረተሰብ ክፍል ያለዉን የማጣት ስጋት
- ከአንዱ የህዝባችን አካል የወጡ ሊሂቃኖች የሌሎች ተመሰሳይ ልሂቃን መውጣት መጀመር እና ሌሎች እይታዎች እና አስተሳሰቦች በመምጣታቸው የቆየው አስተሳሰብ challeng ውስጥ መግባቱ ያልተመቻቸው

እነዚህን ከላይ የዘረዘርናቸውን እና ሌሎች እነዚህን የመሳሰሉ ምክንያቶች በማንኛውም ማህበረሰብ ከአንድ ኡደት ወደ ሌላ ኡደት በሚያደርገው ሂደት ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ ፈተናዎች ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ኡደት ለውጥ ፈላጊ እና ያለው እንዲቀጥል የሚሻው አካል በሚያደርጉት ግብግብ በመታየቱ ሂደቱ ለብዙዎች የግጭት እና ያለመግባባት አብይ ምክኒያት ይሆናል፡፡ ይህ ስር የሰደደ የማህበረሰብ ያለመተማመን ወደ መፍትሄ ሊያመራ የሚችለው የማህበረሰብ አባላት

- **በአካል መቀራረብ  ይጀመ ር ዘንድ ጥሬት ማድረግ** ያለመተማመን እየጎላ በሄደ መጠን ህብረተሰብ ውስጥ ግለሰቦች ሃሳብን መለዋወጥ እና የተለያዩ ሃሳቦችን ከማንሸራሸር መታቀብ ብቻ ሳይሆን በአካልም ይራራቃሉ፡፡  በተወሰኑ ስፍራዎች ላይ በጋራ ላለመገናኘት መወሰናቸውን ተከትሎ የአካል እና የስነ-ልቦና መራራቆች እየጎሉ ይመጣሉ፡፡
- ይህ ስር የሰደደ የማህበረሰብ ያለመተማመን ወደ መፍትሄ ሊያመራ የሚችለው ከሁለቱም የማህበረሰብ ክፍልሎች የመጡ ውጤት ተኮር አካሎች በጋራ ሲሰሩ ነው፡፡ ቡድኖቸም ባለመተማመናቸው በማህበረሰባቸው ላይ የደረሰውን በደል እና አደጋ በጥሞና በመመርመር መስዋዕት ለመሆን እና ህዝባቸውን ለማቀራረብ ያለሰለሰ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ሰዎች ልዩነታቸውን እንዲያጠቡ ከሚገፋፏቸው ነገሮች መካከል በአምባገነኖች የሚወሰዱት አሰቃቂ እና መረን የለቀቁ የጭካኔ እርምጃዎች ናቸው፡፡ በዚህም ተራርቀው የነበሩ ግለሰቦች / ማህበረሰቦች በመሃከላቸው ሰፍሮ የነበረን ያለመተማመን ለመቀነስ በጋራ እንዲሰሩ ያበረታታል ፡፡

እንግዲህ እነኝህን መጥፎ ክስተቶች በመጠቀም ማለትም ከፉ አጋጣሚዎች በመጡ ግዜ ለዛ አፀፋ ለመጣደፍ ሳይሆን የረዥም ግዜ እቅድ አውጥቶ ያንን እንዴት ለዘላቂ መፍትሄ በዘላቂነት መጠቀም እንደሚቻል ዕቅድ ማውጣት ይጠይቃል። ከዛም በተጨማሪ ይህ ወደ አንድነት የመምጣት እና ያለመተማመንን የማስወገድ አጋጣሚ የተከሰተበትን ሁኔታ ተከትሎ በጋራ ለማንቀሳቀስ የሚቻልበትን ረዥም እቅድ መንደፍ ነው። ለዚህ ዋንኛው መሰረቱ motivated የሆኑ ከሁለቱም የህብረተሰብ ክፍሎች የተነሱ አካላት ችግሩ መኖሩን በትክክል መቀበላቸው ነው። መጀመርያ የችግሩን መኖር መቀበል እና ለችግሩ እውቅና መስጠት መሰረታዊ ጉዳይ ነው። ይህን ካደረጉ እሱን ተከትሎ የችግሮችን ቅደምተከተል በማስፈር የትኛውን ችግር ቀድሞ መፍታት መፍትሄውን ሊፋጠን እንደሚችል ወይም በርካታ ደጋፊዎች ሊኖሯቸው እንደሚችሉ ጥናት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

እንግዲህ አንድ ማህበረሰብ የዚህ አይነት ስር የሰደደ ያለመተማመን ችግር ያለበት መሆኑ ከታወቀ የተለያዩ ተቋማት ይሁኑ ግለሰቦች ለችግሩ እልባት ለማግኘት ሲባል የሚጫወቱት ሚና ይኖራል። ይህንንም በተመለከተ ከዚህ በታች የተቋማት እና የግለሰቦችን ድርሻ ለመዳሰስ እንሞክራለን።

1. <u>የትምህርት ተቋማት ሊጫወቱት የሚገባ ሚና</u>

የትምህርት ተቋማትን ስርዓተ-ትምህርት ሲቀርፅ አቀራረፁ ጥንቃቄ የተሞላበት ሊሆን ይገባዋል። የትምህርት ተቋማት ያለ አድሎ እና ወገንተኝነት በብሄሮች ይሁን በተለያዩ የእምነት ስርአቶች እና አስተሳሰቦች ዙርያ ተከባብሮ ፣ ተቻችሎ እና ተግባብቶ ሊኖር የሚችልን ትውልድ በመቅረፁ ሂደት ሊጫወቱት የሚገባ ሚና ከፍተኛ ነው።

ይህ ማለት የትምህርት ተቋማት ዘንች ሊከተሉት የሚገባን እምነትን ይመርጣሉ ሳይሆን እያንዳንዱ የእምነት ተከታይ እንደ ሃገሪቷ ዜጋ እምነቱን የመተግበር መብት እና ነጻነት ያለው መሆኑን እና ያም በህገ-መንግስት የተደነገገ የዜግነት መብት መሆኑን ማስተማር ነው። በዚህም ትውልድ የዜጎችን እኩልነት በመማር የሁሉንም እኩልነት ለሚያረጋግጥ ስርዓት እና ደንብ ተገዢ የመሆንን ባህል እያጎለበተ የሃገር መተዳደርያ ሆኖ የተቀረፀን ፣ የሚቀረፅን እና የሚሻሻልን ህግ ጨምሮ ማክበር የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ በአእምሯቸው ማስረፅ ይጠበቅበታል። ይህ እቅድ በስራ ላይ ከዋለ በተሻለ መልኩ የለላዉን መብት ሊያከብር እና ሊያስከብር የሚችል ትውልድ ማፍራት እንደምችል ተስፋ ይደረጋል ።

ያለው መንግስት የአገራችንን ህገ መንግስት ስለማያከብር ይህን በተመለከተ አንዳንድ ሰዎች ህገ መንግስቱን ከሰፈረበት ወረቀት ዋጋ በላይ የማያወጣ ነው እያሉ ስተቹ ይደመጣሉ። ልስተዋል የምገባው ጉዳይ ሲጀመር ማንኛውም አስተሳሰብ የሚቀረፀው በወረቀት ላይ ነው። ይህ በወረቀት የተነደፈው ሃሳብ በህዝብ ዘንድ ተቀባይነትን እያገኘ በሄደ ቁጥር እና በተማሪዎች ፣ በቤተሰብ እና በማህበረሰብ ልቦና ውስጥ እንዲሰርፅ በተደረገ ግዜ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት መሰረት ይጥላል። ይህ ግን ረዥም ግዜ የሚፈልግ ሂደት መሆኑን ማንም ሊክደው አይችልም። ይህን መሰል እርምጃዎች የዴሞክራሲ ፅንሰ ሃሳብን ነብስ እንዲዘራ በማድረግ ህዝቦች በህግ ፊት እኩል ናቸው የሚለውን የዜግነት መብት ከለጋ እድሜ ጀምሮ ማስረፅ እጅግ ወሳኝነት ያለው ጉዳይ በመሆኑ የትምህርት ተቋማት ድርሻ ከፍተኛ ነው።

<u>የቤተሰብ ድርሻ</u>

በቤተሰብ ደረጃ ቤተሰቡ ውስጥ ወላጆች ልጆቻቸው የሌሎችን እምነት ፣ አስተሳሰብ ይሁን ምርጫን ማክበር እንደምኖርባቸው ማስተማር የምጠበቅባቸው ሲሆንማለትም ስሌሎች ፣ እምነት ሌላ በልጆቹ ፊት ከማያንጓጥጥ ከማያሾፍ እና ከማስተናንስ) መቆጠብ ይኖ ርባቸዋል

ቤተሰብ በበት ውስጥ ልጆች በትምህርት-ቤት ገበታቸው ደግሞ ዜግነት ህዝቦችን እኩል የሚያደርግ የእኩልነት መብት ነው ሚለውን ሲማሩ በዳይ የማይሆኑ እና ለህግ ተገዥ የሚሆኑ መሪዎችን ማፍራት ይቻላል። ከዚህ አንጻር የቤተሰብ ድርሻ ትልቁን ስፍራ ቢይዝም እነዚህ ቤተሰቦች በራሳቸው ይህን አይነት አስተሳሰብ በልጆቻቸው አዕምሮ እንዲያሰርፁ ትልቁን ድርሻ የሚይዘው አሁንም የሚዲያው ፣ የስነፐበብ ፣ ፊልም እና ሌሎች መድረኮች ነው። ይህ የአስተሳሰብ እድገት እጅግ ረዥም እና ትውልድ አልፎ የሚመጣ ትግል በመሆኑ ይህ የዜጎች እኩልነት ትምህርት አስተሳሰብ ስር እንዲሰድ የሁሉም ድርሻ ይሆናል ማለት ነው።

<u>የሃይማኖት አባቶች እና ተቋማት ድርሻ</u>

የሃይማኖት ተቋማት በዚህ ረገድ ሊጫወቱት የሚገባ ድርሻ እጅግ ከፍተኛ ነው። ሰዎች የሚኖራቸው የእምነት ተቆርቋሪነት የሚሰበከውም ሆነ የሚማሩት በነዚህ የእምነት ቦታዎች ውስጥ ነው። በመሆኑ እነዚህ ባለ ድርሻ አካላት የህብረተሰብን ተግባብቶ የመኖር የተለያዩ እምነቶች እንዴት በአንድነት በጋራ ተከባብረው እና ተስማምተው harmoniously ይኖራሉ የሚሉ ትምህርቶችን ማስተማር ይጠበቅባቸዋል። ሰዎች እምነቶችን ተከላካዮች መሆናቸው ቀርቶ እምነታቸውን የመተግበር የግል እና የቡድን የዜጎች መብት መሆኑን በልቦናቸው ያላሰረፁ ግዜ ከነሱ የተለየ እምነት ያለውም አካል ከሱ እኩል ዜጋ መሆኑን ስለሚረዳ እና የሁሉም ከለላ የሆነውን የጋራ ህግ በጋራ መጠበቅ የሚለውን የማስተማር የእምነት ቦታዎች ድርሻ ይሆናል ማለት ነው።

ሌላው የእምነት ተቋማት ሊጫወቱት የሚገባ ሚና በማህበረሰብ ውስጥ የሚከሰቱ አካባቢያዊ እና ሃይማኖታዊ ግጭቶችን የሚፈቱበትን መንገድ መቀየስ። የአንድ ወይም የተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ የማህበረሰብ አካላት የዚህ አይነት ግጭቶች ሲነሱ ወደ ፍርድ ቤት እና ፖሊስ ጋር ከመሄድ በነዚህ የእምነት አባቶች ጉዳዮችን በመያዝ እርቅ እና ሰላም የሚገኝበትን መንገድ መፈለግ። ይህ ግለሰቦችን በማህበረሰቡ የተከበሩ የእምነት አባቶችን በማክበር ከተሳሳተ የግል ውሳኔ የጥፋት እርምጃ እንዲቆጠቡ ያግዛል። በዚህም ግለሰቦች ከህግም ሆነ ከእምነት አባቶች የሚመጣውን ማህበራዊ ጫና በመፍራት ወደዚህ አይነት የተሳሳተ ጎዳና ከመሄድ ይታቀባሉ።

<u>የሚዲያ ተቋማት ድርሻ</u>

ሚዲያ ህብረተሰብን ወደ ሰላምም ሆነ ወደ አመፅ የማነሳሳት አቅሙ እጅግ ከፍተኛ ነው። መረጃ በዘመናችን እጅግ የጎላ ስፍራ ባለው ባአሁኑ ወቅት ማህበረሰብን ወደ አላስፈላጊ ግጭቶች ወይም ያለመተማመኖች እንዲያመሩ የሚያደርጉ አስተሳሰቦችን በጥንቃቄ የማየት ከፍተኛ ድርሻ ይኖርባቸዋል። ለዚህም የሚረዳ ከተለያዩ የእምነት ይሁን የብሄር ተዋፆ ያለባቸውን ቡድኖች በማዋቀር እና አማካሪዎችን በማፈላለግ ለሚያስተላልፏቸው ፕሮግራሞች የሃገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ተፈጥሯዊ ፣ ባህላዊ እና እምነታዊ ጉዳዮችን በሚመለከት ከሃገራችን ነባራዊ ሆኔታ ጋር የማይገጥሙን ፕሮግራሞች ይሁኑ ሌሎች ተዛማጅ ሁኔታዎችን ከመቀላቀል በመቆጠብ ነው። ሌላው ሚዛናዊ የሆኑ ዘገባዎችን በማቅረብ እና ስለመቻቻል ሆነ በልዮነት ውስጥ እንዴት በጋራ መኖር እንደሚቻል የሚያሳዩ መቀራረብን እንዴት ማጎልበት ይቻላል የሚሉ አስተሳሰቦች ዙርያ ያጠነጠኑ ዝግጅቶችን እና ፕሮግራሞች ማስተላለፍ።

አብሮነትን ማጎለበት የሚቻልበት አንዱ እርምጃ የተሰበጣጠረ ማህበረሰብን በህግ ጥበቃ ስር እንዴት ያለግጭት ህዝቦች እንደምኖሩ ማሳየት እና ማጉላት። በምሳሌነት ልጠቀሱ የምችሉ ሃገራትን በማፈላለግ ለነዚህ እሴቶች የጎላ ስፍራ በመስጠት መስራት። ከላይ እንደጠቀስነው በቤተሰብ ውስጥ የሚጀመረው የመቻቻል እና የመከባበር የጋራ እሴቶች ላይ እንዴት በልዩነት ውስጥ አንድነትን መፍጠር ይቻላል የሚለውን በግንባር ቀደምትነት ሚዲያዎች ሊጫወቱት የሚገባ ድርሻ ይሆናል ማለት

ነው። ሚዲያ ስንል በመረጃ መስጫዎች ብቻ ሳይሆን ፣ ስነ ፅሁፎች ፣ የቲያትር መድረኮች ፣ ሲኒማዎች እና የመሳሰሉ የህብረተሰብን ስሜት በሚኮረኩሩ መድረኮች እነዚህን የሰላም እና የአብሮነት ስሜት የሚፈጥሩ ተግባራትን ለነዚህ ተግባራት ቢጠቀሚቸው ውጤታማ ስራ መስራት ይቻላል ብለን እናምናለን።

የግለሰቦች ሃላፍትና

ያለመተማመን ለመቅረፍ በግለሰቦች ደረጃ ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች፡- በቅድምያ ስር የሰደደ ያለመተማመን ያለበትን ህብረተሰብን ለማቀራረብ የሚደረገው ስራ የሚጠይቀው ትዕግስት ከፍተኛ መሆኑ ታውቆ በቂ ዝግጅት ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው። በተጨማሪ

- ውጤት ለማየት ያለመጣደፍ
- በየደረጃው ማዳለጥ እንዳለ እና ወደፊት ከተኬደ ቡሃላ ማፈግፈግ/መንሸራተት እንዳለ ተገንዝቦ በትዕግስት እና በፅናት ችግሮችን በየደረጃቸው ለመቅረፍ መሞከር እጅግ አስፈላጊ በመሆኑን እያንዳንዱ ወገን አምኖ ሊቀበል ይገባል/ወይም የስነ ልቦና ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባታል።

በግለሰብ ደረጃ በመጀመርያ ችግር መኖሩን በትክክል ማመን ይጠበቅበታል። አንድ ግለሰብ ሆነ ብዙ ግለሰቦች ችግር መኖሩን ካላመነ/ኑ ወደ መፍትሄ ሊራመድ አይችልም። ስለዚህ ማህበረሰብን ያራራቁ አንዱ ሌላኛውን እንዲጠረጥር ያደረጉ ችግሮች ስለመኖራቸው ማወቅ እና ለዛ መፍትሄ ለመሻት ዝግጁነትን ማሳየት ያስፈልጋል። ለችግሮች እውቅና ከተሰጠ ቡሃላ ችግር ተብለው የሚታሰቡትን ከተለያዩ ማዕዘናት የህብረተሰብ ክፍሎች እንድመለከቱ በመርዳት። በማስከተል በግልፅነት እና አድሎ በሌለበት መልኩ ችግሮች ከሁሉም አቅጣጫ ሁሉም ወገን በዝርዝር እንድያያቸው ማገዝ ችግር ላይ ለመነጋገር ብቃት የሚኖርበትን ሁኔታ ማመቻቸት።

በሶስተኛ ደረጃ በወጡት ዝርዝር የችግር አይነቶች ቅደም ተከተል ላይ ለመነጋገር ይቻል ዘንድ ዓላማን ግልፅ ማድረግ ነው። በዚህም የሚደረጉ ውይይቶች እና የሚደረጉ ስብሰቦች ሁላ ውጤት ተኮር መሆናቸው እና መፍትሄ ለማምጣት እንጂ ችግር ለማባባስ እንዳልሆነ ማሳወቅ። ሁሉም ወገን ውይይቶችን በሚጀምርበት ግዜ የሚያነጣጥረው መፍትሄ ላይ እንዲሆን መመካከር እና መተማመን ደረጃ ላይ መድረስ ያስፈልጋል። ይህ የሚያስፈልግበት ዋናው ምክንያት ጣት መቀሳሰርን ለማቆም እና አንዱ ሌላኛውን ለመርታት የሚመጣበትን የሽንፈት እና የኪሳራን ጉዞ ለማስቀረት ይረዳል። ይህ ካልታረመ ዳግም ለመመለስ አስቸጋሪ ወደሚሆንበት ችግርን የማክረር እና የመረራራቅ ደረጃ ስለሚያመራ ሁሉም ወገን በጥሞና ሊያስብበት ይገባል።

ስለሆነም ወደ ውይይት መድረኮች ስንመጣ ለማሸነፍ ሳይሆን መፍትሄ ለመፈለግ መሆን እንዳለበት ሁላችንም በልቦናችን ልናሰርፅ ይገባል። ውይይቶች ስኬታማ ይሆኑ ዘንድ ቀለል ካሉ ችግሮች መጀመር አስፈላጊ ነው። ብዙ ወገኖች በቀላሉ ሊፈቱ ይችላሉሉ ብለው ሚያስቡዋቸው እና የሚስማሙባቸው ችግሮች ላይ በቅድምያ በመነጋገር ደረጃ በደረጃ መተማመን እየጎለበተ እና ስር እየሰደደ እንዲመጣ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ቀለል ያሉትን ችግሮች መፍታት ከተቻለ በሂደት ወደ አስቸጋሪ እና አሻሚ ወደሆኑ አነታራኪ ጉዳዮች ማምራት ይቻላል። ነገርግን እጅግ አወዛጋቢ ከሆኑ ችግሮች መጀመር ለሚደረገው ጥረት ውድቀት ስለሚያስከትል ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል። ባየነው እና በልምዳችን ብዙውን ግዜ ውይይቶች የሚጀመሩት እጅግ አስቸጋሪ ከሆኑት ርእሶች ስለሆነ ብዙም

እርምጃ ሳንራመድ መፈረካከስ መጥቶ እንደገና ላንገናኝ ተረጋግመን የተለያየንባቸው አጋጣሚዎች በብዛት ስላሉ ወደዛ ላለመግባት ጥንቃቄ ልናደርግ ይጠበቅብናል።

ውይይቶችን የተቃኑ ለማድረግ የመተማመን አስፈላጊነት በተለያዩ ፀሃፊያን እና ቀና አሳቢዎች ዙርያ ፅሁፎች እየተበተኑ የመነጋገርያ ርእሶች እንዲሆኑ ማድረግ ሌላው የግለሰቦች ሃላፍትና ነው። ስኬታማ የሆኑ የውይይት ስልቶች ፣የመነጋገር እና መቀራረብ ዘዴዎች ምን እንደሆኑ አንዱ ለሌላው ልምድ እንዲያካፍል የሚረዱ ስነ-ፅሁፎች በብዛት እንዲበተኑ እገዛ ማድረግ የዜጎች ሃላፊነት ስለሆነ በዛ መስክ ማበርታት አስፈላጊ ነው። ውይይቱ ቀጣይነት ያለው በሆነ መንገድ እና ለጠላት ቀዳዳ በማይከፍት መንገድ ሆኖ መዳዝን ይፈልጋል። የሶሻል ሚዲያው ሆነ በተለያዩ መድረኮች የሚጻፉም ፅሁፎች ሆነ ተጋብዘው የሚመጡ ግለሰቦች targeted የሆኑ ስራዎችን ብቻ እንዲያቀርቡ ማበረታታት። ለእርቅ ፣ ለመስማማት እና ለመቀራረብ የሚያስችሉ ብሎም የመራራቅን ነቀርሳ ለመንቀል የሚያስችሉ መፍትሄዎችን የሚያቀርቡ ሃሳቦች ላይ ትኩረት ያደረጉ ስነ-ፅሁፎች እና ውይይቶች ላይ እንዲያተኩሩ ማበረታታት እና ወይይቶችን መምራት አስፈላጊ ነው ።

ተጋብዘው ወደ ውይይት መድረኮች የሚመጡ ግለሰቦችም በቀና መንፈስ የመቀራረብ መንፈስን ሊያመጡ የሚችሉ እንዲሆኑ ተደርጎ polarized የሆኑ ግለሰቦችን በማግለል ለመከፋፈል የሚመጡን ድምፆች በመነጠል ላይ ጥረት ሊደረግ ይገባል። ነገር ግን በዚህ አይነት ጉዞ ውስጥ ከፋፋይ የሆኑ ግለሰቦችን በመጋበዝ እና መድረኮችን ለንትርክ እና ለውዝግብ ክፍት የማድረጉ ሁኔታ የማያዋጣ ስለሆነ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል። ከዚህ በተጨማሪ ጉዳዩን ወደ ማህበረሰባችን እንዲወርድ ከተፈለገ እና ውጤታማ ይሆን ዘንድ አክቲቪስቶች ፣ ጦማርያን በድህረ-ገፆቻቸው እና በተለያዩ ስፍራዎች በሚቀርቡበትም ግዜ ትኩረታቸ ለመስማማት እና ጥርጣሬን ለማስወገድ በሚል ርእስ ላይ ያተኮረ ቢሆን የተመረጠ ይሆናል። የሃይማኖት አባቶችም በፀሎት ስፍራዎች ለምእመናን ይህን መልእክት ቢያስተላልፉ እና የስብከቶቻቸው ትኩረት ጥርጣሬን ማስወገድ እና በአንድነት ከሌሎች እምነቶች ጋር በጋራ የመኖር ጉዳይ በሃይማኖትም የተወደደ ስለመሆኑ የማስተማራቸው ሁኔታ በተግባር ወደ ማህበረሰብ የወረደ ስራ ለመስራት ያግዛል።

በተጨማሪም የውይይት መድረኮች በተከታታይ ዘላቂ የሆነ የመተማመን መንፈስ ለማስፈን የሚቻልበትን የውይይት አካሄድ መምረጥ። ግለሰቦችም ቀና አስተሳሰብ ላይ በማተኮር ውጤት የሚያስገኙ ውይይቶች እንዲያደርጉ targeted የሆነ ውይይት ማድረጉ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። የህብረተሰቡን መቀራረብ የማይፈልጉ አካላት የሚያደርጉትን ደባ ለማክሸፍ ይቻል ዘንድ የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶች ዝርዝር ለህዝብ ግልፅ ማድረግ። በዚህም ሰዎች ነቅተው እንዲጠባበቁ ማድረግ ይቻላል። መቀራረቡን የማይፈልጉ ሰዎች ምን አይነት መንገዶች እና ዘዴዎች ከፋፋዮች እንደሚጠቀሙ በመግለፅ ንቁ የሆነ ጥበቃ ተደርጎ በዚህ አይነት የተሰማሩ ግለሰቦችን ማግለል አስፈላጊ ነው። ከዛም በተጨማሪ የከፋፋዮችን ሴራ ለይተው የሚያወጡ ንቁ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በተቀነባበረ መንገድ መረጃ እየተቀባበሉ በዚህ የተሰማሩ ሰዎችን ማጋለጥ እና ከጥፋታቸው እንዲታቀሙ ማስተማር እና መምከር ተገቢ ሆኖ ይገኛል።

እንግዲህ ከላይ ከተዘረዘሩት መረጃዎች መረዳት የምንችለው ከዚህ ቀደም የተጓዝንበት የጉዞ መስመር የማያዋጣ መሆኑን ተገንዝበናል። ማለትም ከፋፋዮች ከፋፈሉን ፣ መንግስት አንድነታችንን ስለማይፈልግ ከፋፍሎን ነው የሚለውን በሶስተኛ ወገን ላይ ያነጣጠረን እርግማን ማውረድ መተው። ከዛ በተጨማሪ ችግሩ ከኛም ጭምር መሆኑን ተገንዝበን በኛ በኩል እርምት አድርገን ላለመከፋፈል ወስነን በዚህ ላይ መስራቱ እጅግ ወሳኝነት ያለው ነው። ነገር ግን ተመልሰን ችግሩን ወደ ሌላኛው አካል ላይ በማዘዋወር ስለከፋፈሉን ተከፋፈልን የሚለው ተራ ምክንያት ስር መደበቅ መሞከር ታጥቦ ጭቃ ስለሆነ ከዛ ተጠብቀን እየተመካከርን ወደፊት መሄድ ነው። እንግዲህ መተማመን ይፀና ዘንድ

እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦች ሰጥቶ መቀበልን መማር ነው። አንዱ ወገን ቀና መንገድ ባሳየ ግዜ ያን ቀና መንገድ ተከትሎ ቀና መንገድ ማሳየት ቀና እርምጃ ነው።

<u>ሰጥቶ መቀበል በጎ ገፅታዎች ለሰላም እና እርቅ</u>

በግለሰቦች ደረጃ የሚጠቀሰው ቀዳማዊ ችግር ሌላኛው አካል በመጥፎ አደጋዎች ላይ ብቻ ባነጣጠሩ ጉዳዮች ላይ መረጃዎችን በማሰባሰብ መሰረተቢስ የሆኑ ጥላቻዎችን እና ፍራቻን እንዲደላደሉ ማድረጋቸው ነው። ይህን ችግር በግልፅ ለመቅረፍ ዝግጁነታቸውን ማረጋገጥ እና ለዛ ስራ መጀመርን ማሳየታቸው ነው። በመሆኑም ይህንን ችግር ለመቅረፍ አካላዊ መቀራረብ እና መተዋወቅ አስፈላጊ ስለሆነ የመቀራረብን እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁነትን ማሳየት ከግለሰቦች የሚጠበቅ የመጀመርያ ደረጃ ሂደት ነው። በአካል መቀራረባቸውም በጎ ገጽታዎችን ለማየት ስለምያበቃቸው ከዚህ ቀደም ይሰሙት የነበረውን የተዛባ ሃሳብ ስህተተኛ መሆኑን በመገንዘብ እውነተኛ የሆኑ መረጃዎችን አሰባስበው በልበሙሉነት ከወገናቸው ጋር እንዲሰሩ የሚያበረታታቸው ይሆናል ። ነገር ግን ሊስተዋል የሚገባው ይህ አይነት አካሄድ ለረዥም ግዜ የተደላደለ ያለመተማመን ባለበት ህብረተሰብ ውስጥ በቀላሉ ወደ ግብ መድረስ የማይቻል ስለሆነ ግለሰቦች ይህንን በማወቅ በትዕግስትና በፅናት ስራቸውን ለማከናወን ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ሌላኛው ነጥብ በሁለቱም ወገን የሚገኙ ግለሰቦች ያለመተማመንን ለማስወገድ በትጋት እንደቆረጡ በግልፅ ማሳወቅ እና ቃል-ኪዳን ማስገባት። ቃል-ኪዳን መግባታቸው ለጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጡ የሚገፋፋቸው በመሆኑ ለክብራቸው ሲሉ ይህንን ሃላፊነት እንዲረከቡ የሚያበረታታቸው ስለሆነ በዚህ ስራ እንደሚገፉበት ተስፋ ይጣላል። በመቀጠልም ከአንድ ወገንም እንኳ በተገባው ቃል-ኪዳን መሰረት ቀዳሚ እርምጃ በመውሰድ ከቃል-ኪዳኑ ጋር የሚጣጣም ድርጊትን መፈፀም መጠራጠርን የሚቀርፍ ስራ ሰርቶ ማሳየት ሌላኛው ወገን በሂደቱ እንዲቀላቀል ስለሚያበረታታ ቀዳሚ እርምጃ የወሰደው አካል በፅናት ከሌላኛው አካል ብዙም ሳይጠብቅ በበጎ ድርጊቱ ቃሉ እና ድርጊቱ ተመጋገበው ተደጋግፈው ማታየቱ ሌላው የሱን አርአያ እንዲከተል ሊያበረታታው ይችላል።

በቀዳሚነት ወደ ተተለመው በጎ እርምጃ ለመሄድ የወሰደው አካል የአፀፋ ምላሽ ወዲያውኑ እንኳ ባያገኝ በጥንቃቄ በበጎ ስራው መግፋት ነው። ይህ ሂደት ሌላኛው ጥርጣሬው የከፋበት ወገኑ መልካሙን ጎዳና እንዲቀላቀል እና ያለመተማመንን በጋራ ተጋግዞ እንዲቀርፉ የሚያስችል ስለሚሆን ትዕግስት እና ፅናት ይጠበቃል። ይህ አይነት የበጎ አርአያነት ስራ መተማመንን ለመገንባት መሰረት ስለሆነ እያንዳንዱ ወገን ይህንን ሃላፊነት ለመወጣት ቃል በገባው መሰረት በፅናት መጓዝ ይጠበቅበታል።

የቃል-ኪዳን እና የድርጊት መጣጣም ብሎም የግለሰቦች በተጠበቁበት መገኘት ሌላኛው ተጠራጣሪ ቢኖር እንኳን መልካም የአፀፋ ምላሽ እንዲሰጥ ያነሳሳዋል። በቀና መንገድ የመተማመንን ግንባታ ማለትም confidence building ላይ በቀዳሚነት የሰራው ወገን አፀፋዊ ምላሽ አርአያ የሆነው አካል ሌላኛው አካል እንዳይበለጥበት እና ብልጠት አገኘሁ ብሎ ያየተፈጠረችውን ግኙነት እንዳያደፈርስ ግንኙነቱ ከተቃረጠ የሚያጣው ነገር ከዛ የላቀ መሆኑን በማሳወቅ ወደ ብልጠት የሚያደላውን ወገን ለጥቅሙ ስሊ እንኳን የመጠራጠ rn መንፈስ እንዲቀርፍ እና ወደ አንድነት እንዲመጣ ጥረት ማድረግ ማበረታታት እርምጃዎችን ማጠንከር ይችላል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ መንገድ ቁልፍ የሆነው የአሰራር ስልት ሰጥቶ የመቀበልን መርህ እንደ መሰረታዊ የመተማመን መገንብያ መቀበል እና ለመቀበል ተግቶ መስራት ነው። አፀፋ ለመስጠት መቀበልን

ልምድ ማድረግ የጎዶሎ ነጥቦችን ስጦታ በመቀባበል የተቀበለው በጎ ምላሽ መልሶ ለሌላኛው ወገኑ ተመሳሳይ ካሳ መክፈል ተአማኒነትን የሚያጎለብት ነው። ስለሆነም ሰቶ መቀበልን የግንኙነቱ መሰረት አድርጎ በፅናት መግፋት እጅግ አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ይህ አይነት አሰራር ከባህል ጋር ሊጋጭ ይችል ይሆናል። ሰዎች ስለሰጠህ እንዲከፈልህ ፈለክ የሚለው መጥፎ የባህል ጉዞ ለዚህ መጥፎ እንቅፋት ሊሆን ይችል ይሆናል። ነገር ግን እንዲህ አይነቱን የባህል እንቅፋት ወደ ጎን በመተው ሰጥቶ መቀበል መሰረታዊ የመተማመን ግንባታ confidence building ገፅታ መሆኑን አምኖ በፅናት መግፋት ይጠበቃል። ሰጥቶ የመቀበል ልምድ ለተሰጠው ነገር ምላሽ መስጠት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በጋራ ለመስራት ትብብርን ለማዳበር ፋይዳ እንዳለው ጥርጥር የለውም። ሆኖም ግለሰቦች ተቀብሎ መስጠትን ልምድ ስለሚያደርጉ ቀድሞ ሰጥቶ በበጎ ልገሳ የመግፋትን አርአያነት ችላ እንዲሉ ስለሚያደርግ ሌላ እንቅፋትነት ሊኖረው ይችላል።

ይህም ማለት ሰጥቶ መቀበል ከሆነ እና አንደኛ አፀፋ እስካልመለሰ ድረስ መጠበቅ ስለሌለበት በአርአያነት ለመመደብ መስጠትን መቀጠል። ሆኖም ይህ አካሄድ የሰጥቶ መቀበልን መርህ የመፍትሄ ሃሳብ ስለሚቃረን ይህ ጥንቃቄ የተሞላበት ጉዞ መጠራጠርን ደረጃ በደረጃ ሊቀርፍ ስለሚችል እንደሌላ አማራጭ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

ከአቡ እምራን

November, 2014